የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.100
Addis Ababa 8th, April 2025

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፺/፳፻፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የምግብ-ሥርዓትና ኒውትሪሽን ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ**

**ገጽ ……………………………………፫ሺ፱፻፶**

**CONTENT**

**REGULATION No. 190/2025**

**ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FOOD SYSTEM AND NUTRITION COUNCIL**

**Page ……………………………………..3950**

## ደንብ ቁጥር ፻፺/፳፻፲፯

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የምግብ-ሥርዓትና ኒውትሪሽን ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ

በሀገር አቀፍ ደረጃ የምግብ ሥርዓት ትራንስፎርሜሽን፣ የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ እና የሰቆጣ ቃልኪዳን ፍኖተ ካርታ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በተሟላ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚመራ፣ የሚያቀናጅ እና የሚያስተባብር የሥርዓተ ምግብ እና ኒውትሪሽን ምክር ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የከተማ አስተዳደሩ የሚያከናውናቸው የትምህርት ቤት ምገባ፣ የቀዳማዊ ልጅነት እና የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ሥራዎችን ከሀገር አቀፍ የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ፕሮግራሞች ጋር በማስተሳሰር አስፈጻሚ ተቋማት እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በማሳደግ ወደ ተግባር ማስገባት የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## REGULATION No. 190/2025

## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FOOD SYSTEM AND NUTRITION COUNCIL

**WHEREAS**, it is found necessary to establish a Council on Food System and Nutrition that would guide, team up and coordinate the transformation of the food system nationwide, the Food and Nutrition Strategy and the Roadmap for the Seqota Declaration in a manner that is complete and effective in city government;

**WHEREAS,** it has become necessary to the city government's work on school feeding, primary childhood, and food security assurance, ties operations to national food system and nutrition programs, increasing the participation of executive institutions and various stakeholders, as it is necessary to establish a coordination system that can put them into action;

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፺፪ መስረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፺/፪ሺ፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"አስፈጻሚ ተቋም"** ማለት የምግብ ሥርዓትና ኒውትሪሽን ሥራዎችን የሚተገብር በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመ የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋም ነው፤

፬. **"ፖሊሲ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ ነው፤

፭. **"ስትራቴጂ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲን ለማስፈፀም የወጣ ስትራቴጂ ነው፤

፮. **"ምግብ"** ማለት ማንኛውም የሚበላና የሚጠጣ ደህንነቱ የተጠበቀና ለሰው ልጅ ጠቃሚ ንጥረ ምግቦችን የያዘ ነው፤

፯. **"የምግብ ሥርዓት"** ማለት አካባቢን፣ ሰዎችን፣ ግብዓቶችን፣ ሂደቶችን፣ መሰረተ ልማቶችን፣ ተቋማትን እና ተዋናዮችን፤ ምግብ አመራረትን፣ ማቀነባበርን፣ ስርጭትን፣ ዝግጅትና አመጋገብን፤ የምግብ ብክነትንና አወጋገድ ተግባራትን ማስተሳሰር ሆኖ የእነዚህ ተግባራት ድምር የሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ውጤቶችን አጣምሮ የያዘ ሥርዓት ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 92 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

1. **<u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as: "Addis Ababa City Government Regulation to Provide for the Establishment of the Food System and Nutrition Council Regulation No.190/2025".

2. **<u>Definition</u>**

Unless the context or phrase otherwise requires in this Regulation:

1. "**City**" means the Addis Ababa City;
2. "**City Administration**" means Addis Ababa City Government;
3. "**Executive Institution**" means an executive institution of the city government, established either by proclamation or regulation, that implements the activities of the food system and nutrition's;
4. "**Policy**" means the food and nutrition policy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
5. "**Strategy**" means a strategy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to enforce food and nutrition policy;
6. "**Food**" means that any one that eats and drinks is safe and contains essential n 3952 for humanity;
7. "Food System" means environment, people, resources, processes, infrastructure, institutions and actors; food production, processing, distribution, preparation and nutrition; it is a system that combines social, economic and environmental outcomes that are the sum of these activities, as a means of linking food waste and disposal activities;

፰. **“ኒውትሪሽን”** ማለት የምግብ መመገብን፣ መፈጨትን፣ በሰውነት ውስጥ መዋሃድንና የንጥረ-ምግቦች ጥቅም ላይ መዋልን ይህም ውህደት ለሰውነት አካላዊና አዕምሮአዊ ዕድገትና መዳበር፣ በሽታ የመከላከልና የመቋቋም ሂደትን የሚያካትት ነው፤

፱. **“የሰቆጣ ቃል ኪዳን”** ማለት ሀገር በቀል ቃል ኪዳን ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ፪ሺ፯ እስከ ፪ሺ፳፪ ድረስ እድሜያቸው ከ፪ ዓመት በታች በሆኑ ህፃናት ላይ መቀንጨርን ዜሮ ለማድረስ በኢትዮጵያ መንግስት የተገባ ቃል ኪዳን ነው፤

፲. **“መቀንጨር”** ማለት አስከፊ በሆነ ወይም በተደጋጋሚነት በሚከሰት የተመጣጠነ የምግብ እጥረት፣ ተደጋጋሚነት ባለው ህመም በመጠቃት እና በቂ የሆነ የሥነ ልቦና፣ ማህበራዊ ምክር እና ማነቃቃት እጥረት ምክንያት ከጽንሰት ጀምሮ የሚከሰት ስር የሰደደ የሥርዓተ-ምግብ ችግር ነው፤

፲፩. **“ፍኖተ ካርታ”** ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽ ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ መንግስት ያጸደቀው እና በነባራዊ ሁኔታ እየተናበበ የሚተገበር ፍኖተ ካርታ ሲሆን በዚህ አግባብ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፍኖተ ካርታ እና የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታ ነው፤

፲፪. **“አባል”** ማለት በየደረጃው የሚዋቀር የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ውስጥ ምክር ቤት አባል ነው፤

፲፫. **“ሰው”** ማለት በተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፬. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በከተማ እና በክፍለ ከተማ ደረጃ በሚቋቋሙ የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሬሽን ምክር ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

8. “**Nutrition**” means food intake, digestion, in-body assimilation and nutrient utilization which involves fusion for physical and mental growth and development of the body, immune and resistance process;

9. “**The Seqota Declaration**” means an indigenous declaration, a nationwide declaration made by the Ethiopian government to zero stunting of malnutrition on children under the age of 2 from 2015 to 2030;

10. “**Malnutrition**” means a chronic nutritional disorder that occurs since conception due to a maladaptive or recurrent malnutrition, being affected by recurrent pain, and a lack of adequate psychological, social counselling, and stimulation;

11. “**Roadmap**” means a roadmap adopted by the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to address the nationwide food system and nourish problems in a phased manner, and implemented while existing, in this appropriate way the Seqota Declaration roadmap and a roadmap for the Ethiopian Food System;

12. “**Member**” means is a member of the council in Food System and Nutrition, which is set up at every level;

13. "**Person**" means any natural or juridical person.

## 3. <u>Gender Expression</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

## 4. <u>Scope of Application</u>

This Regulation shall be applicable to Food System and Nutrition Councils that are established at City and Sub City level in the Addis Ababa City government.

## ክፍል ሁለት

## ስለመቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት እና አባላት

**፭. ስለ መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፤

፫. ምክር ቤቱ በምክትል ከንቲባው ይመራል፡፡

**፮. የምክር ቤቱ አደረጃጀት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. የማዕከል እና የክፍለ ከተማ ምክር ቤት፤

፪. የከተማው አስተዳደር የጤና ቢሮ የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

**፯. የከተማ ምክር ቤት አባላት**

፩. የከተማ ምክትል ከንቲባ ……...........ሰብሳቢ፤

፪. የከተማው አስተዳደር የጤና ቢሮ ኃላፊ .. ፀሐፊ፤

፫. የከተማው አስተዳደር የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ .................……………………. አባል፤

፬. የከተማው አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ ..…..............…..…................................ አባል፤

፭. የከተማው አስተዳደር የትምህርት ቢሮ ኃላፊ …..…..........…………………………. አባል፤

፮. የከተማው አስተዳደር የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ................................. አባል፤

፯. የከተማው አስተዳደር የንግድ ቢሮ ኃላፊ ……...........………..……..………………አባል፤

፰. የከተማው አስተዳደር የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ……….............…………………… አባል፤

፱. የከተማው አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ .................…..……………….. አባል፤

፲. የከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ……...........…..…………………….አባል፤

፲፩. የከተማው አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ ……............………………………… አባል፤

፲፪. የከተማው አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር ……………………………………………አባል፤

## PART TWO

## ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, OBJECTIVE, DUTY AND REPONSIBILITY AND MEMBERS

**5. Establishment**

1. The Food System and Nutrition Council of Addis Ababa City Government (hereafter referred to as “**the Council**”) were established under this regulation;
2. The Council's accountability will be to the Mayor;
3. The Council is headed by the Deputy Mayor.

**6. Organization of the Council**

The Council will have the following organisation:

1. Centre and Sub-City Council;
2. The City Government's Health Bureau serves as the Council's Office.

**7. City Council Members**

1. City Deputy Mayor....................... Chair Person
2. Head of the Health Bureau of the City Government......... .........................Secretary;
3. Head of the Industrial Development Bureau of the City Government.................... Member;
4. Head of the Labor and Skills Bureau of the City Government............................Member;
5. Head of the Education Bureau of the City Government................................. Member;
6. Head of the Bureau of Women's Children and Social Affairs of the City Government..................................Member;
7. Head of the Trade Bureau of the City Government................................. Member;
8. Head of the Communications Bureau of the City Government............................Member
9. Head of the Youth and Sports Bureau of the City Government.... ........................Member;
10. Head of the Finance Bureau of the City Government................................. Member;
11. Head of the Plan and Development Bureau of the City Government...... Member;
12. Commissioner of the Public Participation and Voluntarism Coordination Commission of the City Government... Member;

፲፫. የከተማው አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽ…………………. አባል፤

፲፬. የከተማው አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ……… አባል፤

፲፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ………… አባል፤

፲፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድሐኒት ባለስልጣን ኃላፊ ……………. አባል፤

፲፯. የከተማው አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ………............................... አባል፤

፲፰. የከተማው አስተዳደር ስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ……… አባል፤

፲፱. በከተማው አስተዳደር ስር የሚገኙ የሁሉም የክፍለ ከተሞች ዋና ስራ አስፈፃሚዎች ……………..…………………………….. አባል፤

፳. ምክር ቤቱ በዚህ አንቀፅ ከተመለከቱት አባላት በተጨማሪ የሚመለከታቸውን መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን እንደአስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ በአባልነት እንዲካተቱ ሊወስን ይችላል፡፡

፰. <u>የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. ዘርፈ ብዙ የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን የተቀናጀ ዓመታዊ እቅድ ያፀድቃል፤ የምግብና ሥርዓት-ምግብ ተግባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች በቂ በጀት መመደባቸውንና ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፣ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይሰራል፤

፪. የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታ፣ የምግብና ሥርዓት-ምግብ ስትራቴጂ፤ የሰቆጣ ቃል ኪዳን እና ሌሎች ምግብና ሥርዓት-ምግበ ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው የተለያዩ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች እና እቅዶች ትግበራ በአስፈጻሚ ተቋማት እንዲከናወን ያስተባብራል፤ ዋና ዋና የአፈፃፀም ጠቋሚዎችን ይገመግማል፤ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመለየት ውሳኔ ይሰጣል፤

13. Commissioner of the Fire and Disaster Risk Management Commission of the City Government.......... Member;
14. Commissioner of the Farmers and Urban Farming Development Commission of the City Government... Member;
15. Director General of the Water and Sewerage Authority of the Addis Ababa City Government.... Member;
16. Head of the Food and Drug Authority of Addis Ababa City Government... Member;
17. Director General of the Feeding Agency of the City Government... Member;
18. Head of the Strategic Programs Management Office.... Member;
19. Chief Executives of all Sub-Cities under the city government...... Member;
20. In addition to the Members considered in this Article, the Council may also decide to include the relevant governmental and other stakeholders as required by the Council as Members.

8. **<u>Duty and Responsibility of the Council</u>**

The Council will have the following duty and responsibility:

1. Multifaceted food systems and neutrinos approve an integrated annual plan, ensuring that food and nutrition functional sector offices are budgeted enough and properly used for the intended purpose, which it monitors, works to ensure accountability;
2. Food System Roadmap; Food and Nutrition Strategy; Provides Seqota Declaration and other Contributions to Food and Nutrition Coordinates the Implementation of Various Strategies, Programs and Plans to be carried out by Executive Institutions; It evaluates major performance indicators; and makes decisions on identifying challenges facing them;

፫. የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን አተገባበር ከቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ጋር ተጣምሮ መሰራቱን ይከታተላል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤

፬. በምግብ-ሥርዓት ፍኖተ ካርታ፣ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂ፤ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ለማስፈፀም የሚረዱ የማህበረሰብ የግንዛቤና ንቅናቄ፤ የአቅም ግንባታና የሀብት ማሰባሰብ ስልቶች እንዲቀየሱ እና እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፭. በሁሉም የምግብ ሥርዓትና ኒውትሪሽን አስፈጻሚ ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን አስፈጻሚ ተቋማትን ክትትል ያደርጋል፤

፮. በክፍለ ከተማ አስተዳደር ለተቋቋሙ ምክር ቤቶች ድጋፍ ያደርጋል፤

፯. እንደአግባብነቱ በከተማ ወይም በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ አስተዳደር የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም ድጋፍ ያደርጋል፣ ተግባርና ኃላፊነቱን ይወስናል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፰. ለምግብ-ሥርዓት ፍኖተ ካርታ፤ ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂ፣ ለሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ የሚያግዙ ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፱. የምግብ ሥርዓትና ኒውትሪሽን ሥራዎችን የሚደግፉ ከተማ አቀፍ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሥርፀት ተቋማት እንዲጠናከሩ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲. በከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ ወረዳዎች የማህበረሰብ አቀፍ መማማሪያና ሰርቶ ማሳያ እንዲቋቋምና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፲፩. የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ፕሮግራሞች ለሥርዓተ-ፆታ እና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጡ ሆነው መቀረፃቸውን እና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተማ አስተዳደሩ የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ማስተባበሪያ አካል እንዲደራጅ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ መደራጀቱን ያረጋግጣል፤

3. It tracks whether the implementation of the Food System and Nutrition is combined with the Early Childhood Development Program; it provides support;

4. In the food-system roadmap, food and nutrition strategy; community awareness and activism that help to enforce a Seqota Declaration; and capacity-building and resource-raising strategies that lead to their being designed and implemented;

5. It also monitors executive institutions, ensuring that coordination is implemented between all food system and nutrition executive institutions and other stakeholders;

6. It provides support to Councils established by the Sub City government;

7. As appropriate, it supports the establishment of a technical committee in a City or Sub City or Woreda administration, determines its duty and responsibilities, and monitors their implementation;

8. A roadmap for food-systems; it will lead to the expansion of best practices that will help with food and nutrition strategy, for the implementation of the Seqota Declaration;

9. It supports the strengthening of city-wide research and technology system facilities that support food systems and operations;

10. In the city administration, community-based consultancy and work in various Woreda's will lead to the establishment and expansion of displays;

11. It ensures that food system and nutrition programs are designed and implemented as responsive to gender and environmental concerns;

12. When necessary, it would set the direction for a coordination body of food systems and neutrinos to be organized by the city government, ensuring its organization;

፲፫. ምክር ቤቱ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፱. <u>የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ሰብሳቢው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የምክር ቤቱን አባላት ለስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውን ይመራል፤

፪. የምክር ቤቱን ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፤

፫. የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

፬. የምክር ቤቱን ሥራ ለማከናወን የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

**፲. የ<u>ምክር ቤቱ ፀሐፊ</u>**

ፀሐፊው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. ሰብሳቢው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ለሰብሳቢው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፤

፪. የቴክኒካል ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል፤

፫. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል፡፡

**፲፩. <u>የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ቴክኒካል አማካሪዎች ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የምግብ ሥርዓት እና ኒውትሪሽን ቴክኒካል አማካሪዎች ቡድን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. የምክር ቤቱን አባላት የጥሪ ደብዳቤዎች በማዘጋጀት ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ ያስፈርማል፤ ያሰራጫል፤

፪. የምክር ቤቱን የስብሰባ አጀንዳዎች ቀድሞ ለሰብሳቢው ያሳውቃል፤

፫. የምክር ቤቱን ቃለ ጉባኤ እና ዶክመንቴሽን እንዲያዝና እንዲደራጅ ያደርጋል፤

፬. ዕቅድና ሪፖርቶችን ከምክር ቤቱ አባላት ቀድሞ ይሰበስባል፤ ያደራጃል ያቀርባል፤

፭. የተሰጡ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፤

13. The Council carries out additional taskss to help carry out its objectives.

**9. <u>Duty and Responsibility of the Chairman of the Council</u>**

The Chairman shall have the following duty and responsibility:

1. He calls the Council Members for a meeting, where he presides over the meeting;
2. He oversees and coordinates the work of the council;
3. It sets forward focus areas;
4. It carries out other related tasks that help to carry out the work of the Council.

**10. <u>Deputy Secretary of the Council</u>**

The Secretary will have the following duty and responsibility:

1. When the Chairman is absent or unable to perform the work, he replaces the Chairman and carries out the powers and duties conferred upon the Chairman by Article 9 of this Regulation;
2. He serves as the Chairman of the Technical Committee;
3. It carries out the other tasks provided by the Chairman.

**11. <u>Duty and Responsibility of the Food System and Nutrition Technical Advisors Group</u>**

A group of technical advisors for the Food System and Nutrition will have the following duty and responsibility:

1. It produces the call letters of the Council Members and presents them to the Head, signing and distributes them;
2. It informs the Chairman ahead of time of the Council's meeting agendas;
3. It would have the council's minutes and documentation organized to be entertained;
4. It pre-collects plans and reports from Members of the Council, organizes and presents them;
5. It tracks the applicability of dedicated forward focus areas;#

፮. ለፌደራል የሚላከውን የተጠቃለለ ሪፖርት አደራጅቶ ለሰብሳቢው በማቅረብ በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፣

፯. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፪. <u>የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባውን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚያካሂድ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል፣

፪. የምክር ቤቱ ስብሰባ ሊካሄድ የሚችለው ከምክር ቤቱ አባላት ግማሽ በላይ ሲገኙ ነው፣

፫. የመደበኛ ስብሰባዎች አጀንዳ ወይም የውይይት ሰነዶች ስብሰባ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ ለምክር ቤቱ አባላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

፬. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በዕለቱ ለውይይት የሚቀርብ ተጨማሪ አጀንዳ አለ ብሎ ካመነ ማቅረብ ይችላል፣ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ የመወያያ አጀንዳ ይሆናል፣

፭. የምክር ቤቱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፣ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

፮. የምክር ቤቱ አባላት በመደበኛና በአስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ ተወካይ መላክ የሚችሉት ከምክር ቤቱ ሰብሳቢ ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ ይሆናል፣

፯. ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. <u>የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አደረጃጀት</u>**

፩. የየክፍለ ከተማ ምክር ቤት በዚህ ደንብ መሠረት ተደራጅቷል፣

፪. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩ የክፍለ ከተማ ተቋማት ኃላፊዎች የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አባላት ይሆናሉ፣

፫. የክፍለ ከተማ ምክር ቤት በምክትል ሥራ አስፈጻሚ የሚመራ ሲሆን ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ ይሆናል፣

6. It would organize the bundled report to be sent to the federal and present it to the Head of the Health Bureau to be delivered at the time;

7. It carries out other duties provided by the chairman.

**12. <u>Meeting Procedure of the Council</u>**

1. The Council holds its regular session twice a year and may convene emergency meetings as required;
2. A meeting of the Council can be held when more than half of the council members are present;
3. The agenda of regular meetings or the meeting of discussion documents will make it available to the Council to allow for allowances to be delivered before the meeting is held;
4. Any Member of the Council can present if they believe there is an additional agenda for discussion that day; when supported by a majority vote, it will be the agenda for discussion;
5. The Council resolution passes by a vote majority, however, the presiding Chairman will have a decisive vote, as if the members' votes are evenly split;
6. Council Members may only send a representative at regular and emergency meetings when they receive permission from the presiding Chairman of the Council;
7. The Council may also issue its own regulation of meeting procedure.

**13. <u>Organization of the Sub City Council</u>**

1. Sub City Councils are organized according to this regulation;

2. The Heads of Sub City Institutions listed in Article 7 of this Regulation shall be Members of the Sub City Council;

3. The Sub City Council is headed by a Deputy Executive who is accountable to the Chief Executive of the Sub City;

፬. የየክፍለ ከተማው ጤና ጽህፈት ቤት የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሆኖ ያገለግላል፤

፭. ጽህፈት ቤቱ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ፀሐፊ ሆኖ የሚገለግል ባለሙያ ይመድባል፤

፮. የክፍለ ከተማው ጤና ጽህፈት ቤት የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

፯. የክፍለ ከተማው ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ድርሻ ያላቸውን ተቋማትና የማህበረሰብ አደረጃጀቶች አባል እንዲሆኑ ለከተማ ምክር ቤት በማሳወቅ ሊወስን ይችላል፡፡

፲፬. <u>ስለ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የማዕከሉ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፭. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ማንኛውም የሚመለከተው አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፮. <u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ካቢኔው ያወጣው ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፲፯. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ካቢኔው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፰. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

4. The Health Office of the Sub City serves as the Secretary of the Council's Office;
5. The office assigns a professional to serve as Secretary to the borough council;
6. The Sub City Health office serves as the office of the Sub City Council;
7. The Sub City Council may decide by notifying the City Council to be members of other constituent institutions and community organizations as required.

14. **<u>Duty and Responsibility of the Sub City Council</u>**

Duty and responsibility of the Centre Council will be the duties and responsibilities of the Sub City Council.

## <u>PART THREE</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

15. **<u>Duty to Cooperate</u>**

Any relevant body has obliged to cooperate in the execution this Regulation.

16. **<u>Inapplicable Laws</u>**

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet does not apply to issues covered by this Regulation.

17. **<u>Power to Issue Directive</u>**

The Cabinet may issue directive to enforce this Regulation.

18. **<u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of April 08, 2025.

**Done at Addis Ababa this 08 th day of April 2025.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**